# አይረሳም!!

(ለታሪካዊዋ የግንቦት ሰባት ዕለት ማስታወሻ)





የዘመናት እምቅ ተስፋ - ጭላንጭሉ የታየባት፣
የሰብዕ መብት ህልውና - ባደባባይ በትዕይንት..፣
በምርጫ ካርድ ጥበብ ምስጢር - ባገር ገኖ የዋለባት፣
የነጻነት ቀንዲል ብርሃን - ተምቧ! ብሎ የበራባት፣
የ«ይቻላል» ምልክቷ - ሕዝባዊነት የድል ብሥራት፣
አይረሳም! ውለታዋ - ዕለተ-ቀን ግንቦት ሰባት፡፡









ፍትህ፣ ሰላም፣ እኩልነት... - በምድሪቱ እንዲያብቡ፣
ለሕዝባዊው የድል ዓርማ - በማለዳ ቃል የገቡ፣
ለዕምነታቸው ፅናት ቆመው - ባደባባይ ሲሟገቱ፣
ቢታሰሩም፣ ቢታረዙም፣ ቢሰደዱም፣ ቢንገላቱ...፣
ባረመኔው ጥይት ናዳ - ቢቀጠፍም ህይወታቸው፣
በልባችን ማኅደር ሐውልት - አይረሳም ታሪካቸው!!











የብርሃን ንጋት ጮራን - የውበት ፀዳል ያልወደደው፣
በከይሲ ጽልመት ሴራው - ለመጋረድ የደፈረው፣
ያምባገነን አንካሴውን - በሕዝብ ቁስል የቸከለው፣
የነጻነት ትግሉን ምዕራፍ - ለመደፍጠጥ የሞከረው፣
እባብ ሆኖ ርግብ ቢመስል - ጭንብል ደፍቶ በግንባሩ፣
አይረሳም! ለዘላለም - ሰይጣናዊ እኩይ ግብሩ፡፡



ታሪካዊ የደስታ ቀን - ደግሞም የሐዘን መጨረሻ፣
ግንቦት ሰባት-ሰባ ሰባት - የመብት ገድል ማስታወሻ፤
መስዋዕትነት ያገር ሲሳይ - የትውልዱ ብሩህ ራዕይ፣
ማኅተም ዕንቁ ወርቅ አሻራ - ለድል ምዕራፍ የሚያበራ፣
የነጻነት ፈለግ ዓርማው - ከፍ ብሎ ሲውለበለብ፣
አይቀሬ ነው ሕዝባዊው ድል - ሰላም፣ ፍትህ፣ ብልጽግና...
በኢትዮጵያችን ዳግም ሊያብብ!!



የ«ይቻላል» ምልክቷ - ሕዝባዊነት የድል ብሥራት፣
አይረሳም! ውለታዋ - ዕለተ-ቀን ግንቦት ሰባት፡፡

ጌታቸው አበራ
ግንቦት 2000 ዓ.ም.
(May 2008)